# የዓባዩ ካድሬ ጨፈረ!



ዓባዩ ዛሬም አበለ፣
ነፍሰ- በላውን ፈታና ለቀቀ፣
መንጋን  ግን ሊያስር ፈተለ፣
ኮረንቲ ገመድ ሸረበ፣
ካድሬ እንደ ውሻ ጩህ አለ፡፡

የሕፃናት ደም ሲደፋ ፀጥ ያለ፣
ደዴሳ በለስ ሲቀላ ያፌዘ፣
አፉን እንደ ቡሐቃ ከፈተ፣
የዓባዩ ካድሬ ቦረቀ፣
ኮረንቲ  በራ እያለ፡፡

የደም ጎርፍ ሲፈስ ጪጭ ያለ፣
ሕዝብ እንባ ሲያዘንብ ዝም ያለ፣
ዓባዩ ሲሰብክ ቧረቀ፣
ካድሬ ዳንኪራ ደለቀ፡፡

አሩግ በጭራቅ ታርደው እያለ፣
ሴቶች ተመንገድ ተጥለው እያዩ፣
ሕፃናት በእሳት ተቃጥለው ሳለ፣
የዓባዩ ካድሬ እንደልማዱ ጨፈረ!
መቀመጫው አማቶ ደነሰ፣
እንኳን ደስ አለህ አያለ፡፡

የግፉ ጥዋ ሞልቶ ፈሰሰ፣
ውሀ ተሰው ደም ወፈረ፣

ወንዙ ሲረጋ ደሙ ጎረፈ፣
ሕዝብ ለሐዘን ዳስ ጣለ፣
የዓባዩ ካድሬ ግን ጨፈረ፣
እንኳን ለሁሉም ሞት አለ፣
ይህ ሁሉ አሽቃባጭ ነግ የለ፡፡

ካድሬ ሲጨፍር እየታረደ ያለ ሕዝብ ጩኸት ያዳምጡ!
https://www.youtube.com/watch?v=wTSuxdV8ACk

በላይነህ አባተ ((abatebelai@yahoo.com)
የካቲት አስራ ሶስት ቀን ሁለት ሺ አስራ አራት ዓ.ም.